## የአዲስ አበባ አርሶአደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን



### አርሶ አደሩን ከከተማው ልማት ጋር
### እያለማች ያለች ከተማ
### አዲስ አበባ

# አርሶ አደሮችን እና የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ከማቋቋምና በዘላቂነት ከማልማት አንፃር ባለፈው ሰባት ዓመታት የተሰሩ ሥራዎች (የለውጡ) ፍሬዎች ቡክሌት









This Lemi Kura Integrated Urban Agricultural Center was officially inaugurated on May 23, 2026, by Her Excellency Adanech Abiebie, Mayor of Addis Ababa.











## የለውጡ ፍሬዎች በፎቶ



- የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል፡ አርሶ አደርን ለማቋቋም የተገነባ (በማዕከሉ በእንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታ፣ በወተት ከብት እርባታ፣ በከብት ማድለብ እና በሌሎች ተያያዥ ስራዎች የተሰማሩ በ104 ማህበራት የተደራጁ ከ500 በላይ የልማት ተነሺ አረሶ አደሮች በስራ ላይ ሲሆኑ አሁን ላይ በቀን ከ32000 በላይ እንቁላል እንዲሁም ወተት በማምረት ለከተማው ነዋሪም ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ ይገኛሉ)።







ትምህርት ቤት፡ በ2015ዓ.ም ለአርሶ አደር ልጆች የተገነባ ትምህርት ቤት (ፕሮጀክት)

- የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፦ በልማት አካባቢዎች የሚገኙ 7,047 አርሶ አደሮች አስተማማኝና ንጹህ የውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

   

- የይዞታ ማረጋገጫ (ካርታ)፦ ከአርሶ አደሩ የመሬት መብት ጋር ተያይዞ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ 19,507 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች ተዘጋጅተው እንዲሰጡ ተደርጓል።

   

- የእንስሳት ልማት ልህቀት ማዕከል፦ በአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ 10 በ14 ሄክታር ላይ የተገነባው ማዕከል የወተት፣ የከብት ማደለቢያ፣ የዶሮ እርባታ፣ የመኖ ማቀነባበሪያና 32 ሱቆችን በማሟላት 104 ማኅበራትንና 540 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ተደርጓል።











- የትምህርት ቤት ግንባታና የሥራ ዕድል፦ በአቃቂ ቃሊቲና በለሚ ኩራ ክፍለ ከተሞች 2 አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን በመገንባትና ግብዓት በማሟላት 300 አርሶ አደሮች በ6 ማኅበራት ተደራጅተው ወደ ሥራ ገብተዋል።











➢ አርሶ አደሮችን ወደ ኢንቨስትመንት ማሸጋገር፡- በግል ይዞታቸው ላይ ሰፊ የልማት ሥራ ማከናወን ለሚችሉ 168 አርሶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲሸጋገሩ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሯል፡፡













- በግል ይዞታ ላይ የሥራ ዕድል ከመፍጠር አንፃር፦ 17,627 አርሶ አደሮች በግል ይዞታቸው ላይ እንዲያለሙ የተደረገ ሲሆን በዚህም ካላቸው ይዞታ ላይ አነስተኛ ቦታ ያላቸው 80 በመቶ እንዲያለሙ እንዲሁም ሰፊ ይዞታ ካላቸው 20 በመቶ ይዞታቸውን ለከተማ ግብርና ስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፤ በዚህም በከተማው በከተማ ግብርና ተሳታፊ ከሆነው 1.2 ሚሊዮን ተጠቃሚ ውስጥ ከተገኘው 478,567.18 ቶን ምርት ውስጥ አርሶ አደሩ በተሰማሩበት ስራ ከራስ ፍጆታ አልፎ የገበያ ማረጋጋት ስራ ላይ ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል፤

አሁን ላይ በከተማው ከሚገነቡ 23 ክላስተሮች መካከል አንዱ ዛሬ የሚመረቀው ክላስተር ግንባታም አርሶ አደሮች ተደራጅተው ወደ ስራ የሚገቡበት ነው።








- ቀጥታ ሰብአዊ ድጋፍ፦ ምንም ገቢ ለሌላቸውና መሥራት ለማይችሉ 1,648 ቀጥታ ድጋፍ ፈላጊ አርሶ አደሮች ለምግብ ፍጆታና ለመጠለያ የሚሆን 312,318,460.00 ብር ድጋፍ ተደርጓል።











- የፋይናንስ፣ የቦታና የማሽነሪ አቅርቦት ድጋፍ፦ የከተማ አስተዳደሩ ብር 985,066,704.99 በጀት በመመደብ ለ5,426 በልማት ምክንያት ለተፈናቀሉ አርሶ አደሮችን በ742 ማኅበራት በማደራጀት የመሥሪያ ቦታ፣ የፋይናንስ/ቀጥታና ተዘዋዋሪ ብድርና የማሽነሪ ድጋፍ ተደርጓል፤ ከተደረገው አጠቃላይ ድጋፍ ውስጥም በአዲስ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ.ማ በኩል የተገዙ የተለያዩ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች (አይሱዙ መኪና፣ ፍሪጅ፣ ሚዛን እና የተለያዩ መሣሪያዎች) በማኅበር ለተደራጁ 156 ልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ተላልፈዋል።











- የአቅም ግንባታ ሥልጠና፦ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ 1,243 ማኅበራትና 6,782 አባላት በቴክኒክና ሙያ ተቋማት በኩል ተግባራዊ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።








- የጋራ ኮንዶሚኒየም ንግድ ሱቆች ስርጭት፦ በማኅበር ለተደራጁ ልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ 233 የጋራ መኖሪያ ሱቆች ተላልፈዋል።








የጋራ ኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት አቅርቦት፦ በከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ መሠረት ለ22,915 ልማት ተነሺ አርሶ አደሮች የጋራ መኖሪያ ቤቶችን የማስተላለፍና የማስረከብ ሥራ ተሰርቷል።














## የልማት ተነሺ መልሶ አርሶ አደር ከማቋቋምና ልማት አንፃር

ባለፉት የለውጥ ዓመታት በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተነሱ አርሶ አደሮችን መልሶ በማቋቋም እና በቀጣይም የከተማው ልማት አካታችነቱን ጠብቆ አርሶ አደሩ አብሮ እንዲለማ ማድረግ የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ በመስራት የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል።

- የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ምዝገባ፦ በልማት ምክንያት የተነሱ 45,527 አርሶ አደሮችና የአርሶ አደር ልጆችን በሦስት ዙር የመለየትና የመመዝገብ ሥራ ተከናውኗል።













## የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

https://bit.ly/4hnxoMs

https://bit.ly/4h2cPVT

https://bit.ly/4gjsu1M

https://bit.ly/4gdXK2o

https://bit.ly/44XrDkt

farmeragr2020@gmail.com

http://aafuadc.gov.et/

https://x.com/AFuadc

https://bit.ly/voiceofaddisurban

https://s.channelcom.tech/6vgYg1